# Finote Ethio-Canadian Information Centre In Toronto

## ፍኖተ ኢትዮ-ካናዳውያን የኢንፎርሜሽን ማዕከል በቶሮንቶ

E-mail: torontofinote@gmail.com


## በቶሮንቶና አካባቢው የሚገኙ ኢትዮጵያኖች በአንድነት ተረባርበው የጃዋርን ስብስባ ከቶሮንቶ ከተማ ሁለት ጊዜ አሠረዙ፤ ተከታትለውም ብራምፐተን ከተማ ተደብቆ ስብስባ ሲያደርግ ደርሰውበት ከፍተኛ ተቃውሞ አሰሙ፡፡

አሸባሪውና ወንጀለኛው ጃዋር መሀመድ በቶሮንቶ ከተማ ለተከታዮቹ ስብሰባ ሊያደርግ በሮያል ዮርክ ሆቴል የያዘውን አዳራሽ መረጃ በቶሮንቶ ከተማ የስልፍ አስተባባሪው ግብረሃይል ሲያስራጭ፣ ቁጥሩ ከፍተኛ የሆነ ኢትዮጵያዊ የተቃውሞ ድምጹን ስልክ በመደወል ለሆቴሉ በማስማቱና ሆቴሉ ከሚችለው በላይ የተቃውሞ ጥሪ ሰለደረሰው የጃዋርን ስብስባ መሰረዙን በማስታውቁ፤ የጃዋር ደጋፊዎች ሌላ ኤርፖርት አካባቢ ዴልታ ሆቴል ይይዛሉ፡፡ በንቃት ሲጠባበቅ የቆየው ኢትዮጵያዊ ይህ መረጃ ቅዳሜ ኖቬምበር 23 ሲደርሰው በጥቂት ሰዓታት ውስጥ ከ1000 በላይ የተቃውሞ የስልክ ጥሪ በማሰማቱ ሆቴሉ ስብስባው እንደማይካሄድ ለማስታወቅ ተገዷል፡፡ ከቶሮንቶም አልፎ በካልጋሪ ከተማ ጃዋርን በመቃወም የተረባረቡት ጀግኖች ኢትዮጵያውያን በትብብር ለሆቴሉ ደውለው ተቃውሟቸውን በማስማታቸው ሆቴሉ ጫናው በዝቶበት ነበር። ፍኖተ ኢትዮ ካናዳውያን የኢንፎርሜሽን ማዕከልም የተቃውሞ ደብዳቤውን በኢሜይል ልኳል፡፡ መሰብሰቢያ ያጣው ጃዋርም ቶሮንቶ እንዳልተሳካለት ሲያውቅ፤ ኖቬምበር 24 ከሰዓት በኋላ ከቶሮንቶ ውጭ ብራምብተን ከተማ የስብሰባ አዳራሽ አሲይዞ ተከታዮቹን በድብቅ ሲሰበስብ መረጃው ኢትዮጵያዊው በደረሰው በጥቂት ደቂቃዎች ውስጥ ምንም እንኳን ለትራንስፖርት አመቺ ባይሆንምና ቢርቅም ወደ ብራምፐተን በመጓዝ በኢትዮጵያን ስንደቅ ዓላማ አሸብርቆ እንደ ፈጥኖ ደራሽ ከተፍ በማለት ተቃውሞውን ለማስማት ችሏል፡፡









በርከት ያሉ የፖሊስ መኪናዎች የአደጋ ጊዜ መብራታቸውን በማብራት መንገዱን ዘግተው ከሰልፈኛው ፊትና ኋል ሆነው ቢጠብቁም፣ ኢትዮጵያውያን በሰለጠነና በጨዋነት ተቃውሟቸውን ሲያሰሙ፣ በአማርኛ፣ በኦሮሚኛና በእንግሊዝኛ መፈክር ሲያወርዱ፣ አገራዊ ዜማዎችን በማዜም የጀዋርን ሽብርተኝነትና ወንጀለኛነት አውግዘዋል፣ መሳሪያ ሆነው ለሚደግፉት ወጣቶችም እንዲያስቡና ለወንጀለኛ መሳሪያ እንዳይሆኑ መልእክት አስተላልፈዋል፡፡

በዚህ የተቃውሞ ስለፍ ላይ የተገኙ ኢትዮጵያውያን በትብብር፣ በአንድነት፣ መረጃ በመለዋወጥና የሚችሉትን ሁሉ በማድረጋቸው፤ እንዲሁም በጊዜው አጭርነት፣ በቦታው እርቀትና በትራንስፖርት ችግር በብዙ ሺህ የሚቆጠሩ ኢትዮጵያውያን ለመገኘት ባይችሉም፤ ሁለቱን ሆቴሎች ስብሰባ በማሰረዝ ላደርጉት ርብርቦሽ ሁሉ ቶሮንቶን አኩርተዋል፡፡ ተፈላጊውን መል ዕከት አስተላልፈወና ተቃውሟቸውን አሰምተው ከመሽ በኋላ ወደ ቶሮንቶ በሰላም ተመልሰዋል፡፡

ኖቬምበር 25 ቀነ 2019 ዓ/ም

ፍኖተ ኢትዮ-ካናዳውያን የኢንፎርሜሽን ማዕከል በቶሮንቶ